የሰ/መ/ቁ.253160
ጥር 27 ቀን 2016 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

ዋዚሞ ዋሲራ

ሡናይት አድነው

አመልካች ፡- አቶ ጌታሁን ባልቻ ቀረቡ

ተጠሪ ፡- ትኬ ሆቴልና ሪዞርት ተወካይ ድልያብ ጀቤሣ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሠራተኛ ክርክር የሚመለከት ሲሆን የአሁን አመልካች ከሳሽ የአሁን ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ ሆኖ በቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የተጀመረ ነው፡፡ አመልካች ባቀረቡት ክስ ከ16/01/2015 ዓ.ም ጀምሮ በተጠሪ ድርጅት ውስጥ በሰው ሀይል አስተዳደርና የሥልጠና ክፍል ሃላፊ የስራ መደብ ተቀጥሬ በወር ብር 20,000.00 እየተከፈለኝ በማገልገል ላይ ሳለሁ በ10/04/2015 ዓ.ም ያለምንም ጥፋትና ያለ ማስጠንቀቂያ በህገ ወጥ መንገድ ከሥራ ያሰናበተኝ በመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.1156/2011 መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ፣ክፍያዎችን የማዘግየት ክፍያ፣ የሥራ ዋስትና ካሳ፣የካሳ ክፍያና ያልተከፈለኝ የ24 ቀን ደመወዜ ጨምሮ ባጠቃላይ ብር 296,000.00 እና የጠበቃ አበል ጨምሮ ወጪና ኪሳራ ይከፈለኝ፤የስራ ልምድ እንዲሰጠኝ በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካች የሥራ መሪ እንጂ ሠራተኛ ባለመሆናቸው በመካከላችን ያለው ግንኙነት ሊዳኝ የሚገባው በፍትሃብሔር ህግ እንጂ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ አይደለም፡፡ አመልካች ለሶስት ወር የሙከራ ጊዜ ተቀጥረው ለቦታው መመጠን ባለመቻላቸው የሙከራ ጊዜው ከማለቁ በፊት በህጋዊ መንገድ የተሰናበቱ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ ውድቅ ሆኖ ወጪና ኪሳራ እንዲከፍሉን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከሰማ በኋላ አመልካች የሥራ መሪ ሆነው ሰራተኞችን የመቅጠር፣ የማሰናበት፣ እንዲሁም የተጠሪን ፖሊሲ የማውጣትና ሥራ ላይ የማዋል ስልጣን ያላቸው መሆኑን ተጠሪ አላስረዱም፡፡ ፍ/ቤቱ እንዲቀርብ የጠየቀውን የሰው ሀይልና የስልጠና ክፍል ሃላፊ የሥራ ድርሻ የሚያሳይ ሰነድ ለፍ/ቤቱ አላቀረቡም፡፡ በተጠሪ ድርጅት ቦርድ በ16/12/2014 ዓ.ም በተሰጠ ውሳኔ የሰው ሃይል ሰራተኛ

መቅጠር እንደማይችል ሰራተኛ የሚቀጠረው ከሥራ የሚሰናበተውና የሚዘዋወረው በተጠሪ ውሳኔ በመሆኑ ፤በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ላይም በአዋጅ ቁ 1156/11 አንቀፅ 2(10) ሥር የተዘረዘረውን እንደሚሰራ ያልተገለጸ በመሆኑ አመልካች የሥራ መሪ ነው በሚል የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ ሆኗል፡፡ አመልካች በአዋጁ ላይ ከተቀመጠው የ60 ቀን የሙከራ ጊዜ በላይ በማገልገላቸው እንደቋሚ ሰራተኛ የሚቆጠሩ በመሆኑና አመልካች ብቃት እንደሌለው እንዲሁም የብቃት ማሻሻያ መሰጠቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ተጠሪ ባላቀረበበት ሁኔታ ያለማስጠንቀቂያ ማሰናበቱ ህገ ወጥ ድርጊት ስለሆነ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣የአገልግሎት ክፍያ፣ካሳ ክፍያ፣ሳይከፈለው የቀረው የ24 ቀን ደመወዝ ክፍያ እና ክፍያ የዘገየበት የሶስት ወር ደመወዝ ክፍያ ባጠቃላይ ብር 221,000.00 እና የጠበቃ አበልን ጨምሮ ወጪና ኪሳራ ተጠሪ ለአመልካች ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጠው ውሳኔ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በአብላጫ ድምጽ ጸንቷል፡፡
ተጠሪ በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝተው ለማስለወጥ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያመለከቱ ሲሆን የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎትም ግራ ቀኙን በማከራከር የቦርዱ ውሳኔ የስራ ምቾት ለመፍጠርና የተረጋጋ የሥራ አከባቢ ለመፍጠር የሰራተኛ ቅጥርና ስንብት በውይይት እንዲሆን ከማለት ውጪ የአመልካች የስራ ድርሻ የሥራ አስኪያጅ መሆን የለበትም ብሎ ያልገደበ በመሆኑ፣የሠራተኞች ስንብት ደብዳቤ ላይ አመልካች እንደፈረመበት በምስክር ቃል የተረጋገጠ በመሆኑና የአመልካች የስራ ድርሻ ስራ አስኪያጅ መሆኑን በሰነድና የሰው ማስረጃ ተጠሪ አስረድቶ ባለበት ሁኔታ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በፍትሃብሔር ህግ እንጂ በአሰሪ ሰራተኛና አዋጅ አይደለም በማለት ያቀረቡትን መቃወሚያ በማለፍ አመልካች ሰራተኛ እንጂ ሥራ አስኪያጅ አይደሉም በማለት የሥር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡ አመልካች ስራ አስኪያጅ ስለሆነ ጉዳዩ በአዋጅ ቁ.1156/2011 መሰረት መታየት የለበትም በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ ለፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የቀረበው በዚህ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ቅር በመሰኘትና ለማስለወጥ ሲሆን የቅሬታ ይዘቱም የሰው ሀይል አስተዳደርና የሥልጠና ክፍል ሃላፊ ሆኜ ብቀጠርም በተጨባጭ ሥራ አስኪያጅ የሚያከናውናቸውን ተግባሮች የማላከናውንና የተወሰነ የሥራ ክፍል ብቻ የምመራ በመሆኑና የተጠሪ ቦርድ ባወጣው መመሪያ የሠራተኞች ቅጥር ፣ዕድገት ዝውውርና ሌሎችም ቦርዱ በሚያቋቁሙ ኮሚቴ የሚከናወን በመሆኑንና በኮሚቴው ውስጥ አመልካች አባል ከመሆን ባለፈ ብቻውን ምንም አይነት ውሳኔ ማሳለፍ እንደማይችል ተወስኖና በዚሁ አግባብ እየተተገበረ ባለበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ስራ አስኪያጅ (ሥራ መሪ) በመሆኑ በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ሊዳኝ አይገባም በማለት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ተሽሮ የክልሉ የወረዳና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ እንዲጸናልኝ የሚል ነው፡፡

የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም የክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሥር ፍ/ቤቶች ያሳለፉትን ውሳኔ የሻረው ማስረጃውን በመመዘን መሆን አለመሆኑን፣ማስረጃውን በመመዘን የተሰጠ ውሳኔ ከሆነ በሰበር ችሎቱ ህጋዊ ስልጣን ስር የሚያርፍ መሆን አለመሆኑን አጣርቶ ለመወሰን ጭብጥ ይዞ ተጠሪም መልስ እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው በሰጡት መልስ አመልካች በሰው ሀብት አስተዳደር የሥራ መሪ ሆነው ለሙከራ ተቀጥረው ሥራቸውን ባግባቡ ማከናወን ባለመቻላቸው የተሰናበቱ በመሆኑ እና ስለ ሥራ መሪ በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/21329፣ 92466 ትርጉም የተሰጠ በመሆኑ በመካከላችን ያለው ክርክር ሊዳኝ የሚገባው በፍትሐብሔር ሕግ እንጂ በአሰሪና ሰራተኛ ህግ አይደለም፡፡ ቦርዱ መቀመጫውን አዲስ አበባ በማድረግ ተጠሪ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙትን ንብረቶች የሚያደራጅ፣የንግድ ስራቸውን የሚመረምርና መንግስት የሚያወጣውን የንግድ አሰራር ፖሊሲ እየተከታተለ ለድርጅቶቹ እገዛ የሚያደርግ እንጂ የእያንዳንዱን ድርጅት ወርዶ ሰው የመቅጠር የማሰልጠን የማሰናበት ሚና የለውም በማለት አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ይፅናልን ብለዋል፡፡ አመልካች በመልስ መልሱ ቅሬታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለ መልኩ ይህን ሲመስል እኛም የግራ ቀኙን አቤቱታና መልስ ለጉዳዩ ከተያዘው ጭብጥና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች አንፃር መርምረነዋል፡፡ እንደመረመርነውም በግራ ቀኙ መካከል ያለውን ክርክር የክልሉ ወረዳና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ግራ ቀኙ ያቀረቡትን ማስረጃ በመመዘን በህጉ መሰረት አመልካች ስራ መሪ የሚያከናውነውን ተግባራት ሲያከናውን እንደነበር ተጠሪ ባለማረጋገጡ አመልካች ሰራተኛ ናቸው፤ ሰራተኛ በመሆናቸው ያለምንም ጥፋትና ማስጠንቀቂያ በመሰናበታቸው ስንብቱ ህገ ወጥ ስለሆነ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁ.1156/2011 መሰረት ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎችን ተጠሪ ሊከፍሉ ይገባል በማለት የሰጡትን ውሳኔ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት አመልካች ስራ መሪ መሆናቸውን ተጠሪ ባቀረቧቸው የሰውና የሰነድ ማስረጃ በተረጋገጠበት ሁኔታ ሰራተኛ ናቸው መባሉ አግባብነት የለውም በማለት የሥር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሻሩን ከቀረበው የውሳኔ ግልባጭ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህም በአመልካች ክስ ላይ ተጠሪ ባቀረበው ተቃውሞ አመልካች የሥራ መሪ ነው በማለት የተከራከረ ቢሆንም በክርክራቸዉ መሠረት ያላስረዱ መሆኑን ማስረጃ መዝኖ ፍሬ ነገርን ለማጣራት ስልጣን ያለዉ ወረዳና ከፍተኛ ፍርድ ቤት አረጋግጦ ዉሳኔ መስጠቱን የሚያሳይ ነዉ፡፡

በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80 (3/ለ) ላይ እንደተመለከተዉ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸዉን ዉሳኔዎች በማረም ላይ የተገደበ ነዉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ደግሞ ማስረጃን መዝኖ ፍሬ ነገርን አረጋግጦ ዉሳኔ መስጠትን እንደማያካትት የሚታወቅ ነዉ፡፡ የኦሮሚያ ክልል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር እንደገና ለመወሰን የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 216/2011 አንቀጽ 26 (1) ላይ እንደተመለከተዉም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ማየት የሚችለዉ በክልሉ ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ዉሳኔ በተሰጠባቸዉ ጉዳዮች ላይ የተፈጸመ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለዉ ብሎ ካመነ ብቻ ስለመሆኑ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ይህ አዋጅ በዚሁ

አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ አንድ ዉሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነዉ ማለት የሚቻልባቸዉን ሁኔታዎች የሚዘረዝር ሲሆን ለሰበር ችሎት ሊቀርቡ የማይገባቸዉን ጉዳዮች ለይቶ በሚደነግገዉ በንዑስ አንቀጽ 3 (መ) ላይ ማንኛዉም የፍሬ ነገር ወይም የማስረጃ አቀባበል ወይም ማስረጃ ምዘና ስህተት የተፈጸመበት ዉሳኔ ለክልሉ ሰበር እንደማይቀርብ ደንግጎ ይገኛል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃን በመመዘን ውሳኔ የመስጠት ስልጣን እንደሌለው በሰ/መ/ቁ.231695 አስገዳጅነት ያለው የህግ ትርጉም ሰቶበታል፡፡

አሁን ወደ ያዝነው ጉዳይ ስንመለስ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት የክልሉን የወረዳና ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሳኔ ለመሻር መሰረት ያደረገው ግራ ቀኙ ያቀረቡት የምስክሮችን ቃልና የሰነድ ማስረጃውን ነው፡፡ ይህም በግልጽ የሚያሳዉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በህገ መንግስቱ እና በህግ ተገድቦ ከተሰጠዉ ስልጣን በላይ በመሄድ ማስረጃን መዝኖ ለዚህ ሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነዉን ዉሳኔ መስጠቱን ነዉ፡፡ ይህም ችሎት የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ ከመመዘን ስልጣን ያለው መሆን አለመሆኑን ለማጣራት በያዘው ጭብጥ ላይም ተጠሪ በግልፅ የሰጡት መልስ የለም፡፡

በመሆኑም የክልሉ የሰበር ሰሚ ችሎት ማስረጃ የመመዘን ስልጣን እንደሌለው በኢፌዴሪ ህገ መንግስት፣ ከላይ በተጠቀሱ አዋጆች እና በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ ፍ/ቤቶች በአስገዳጅነት ሊተገበር የሚገባው በፌ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን አስገዳጅ የህግ ትርጉም ከግምት ሳያስገባ የሰጠው ውሳኔ በፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) (ሀ) (ሸ) ፣10(1)(ሐ) እና 26 (3) መሠረት በዚህ ችሎት መታረም ያለበት መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## ውሳኔ

1.የኦሮሚያ ክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.423872 ሐምሌ 04 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348 (1) መሰረት ተሽሯል፡፡

2.የክልሉ የቢሶፍቱ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ.23043 መጋቢት 19 ቀን 2015 ዓ.ም እና የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.71770 ግንቦት 07 ቀን 2015 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1.መዝገቡ ውሳኔ ያገኘ በመሆኑ ግልባጩ ለግራ ቀኙ ይሰጥ፡፡

2.በዚህ ችሎት ግራ ቀኙ ያወጡትን ወጪና ኪሳራ የየግላቸውን ይቻሉ፡፡

3.መዝገቡን ዘግተን ወደ መዝገብ ቤት መልሰናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፍ/ደ